በነጻ የሚታደል

ቤርያ



የመንፈሳዊ ትምህርት ጋዜጣ ቁጥር 14

እነዚህም [የቤርያ ሰዎች] በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፡- ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው እለት እለት መጻህፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ (ሐዋ 17፡ 11)፡፡

አንቀበልም

አንዳንዶች በአለም የለመዱትን የሰጥቶ የመቀበል መርህ በመንፈሰዊ አገልግሎታቸውም ለመተግበር ይሞክራሉ፡፡ ከእነሱ መካከል ጥቂቶቹ ይህን የሚያደርጉት መርሁ ለምድር ብቻ የሚሰራ መሆኑን ባለማወቅ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎቱን በአለም መርህ ውስጥ አስገብተው ሰማያዊነቱን ሽረው አለማዊ ለማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች አገልግሎት ሲሰጡ በምትኩ በጥሬም ይሁን በአይነት፣ በቁስም ይሁን በሞራል ተመጣጣኝ ምላሽ ይጠብቃሉ፡፡ ይህ መርህ ለሰማይ እንደማይሰራ የገባቸው እና ከመንፈሳዊ ነገር ምድራዊ ረብ በማግኘት ተልእኮ ለሰጣቸው ጌታ ያላቸውን ታማኝነት ማጉደል የማይፈልጉ ደግሞ እንኳን ሊጠብቁ በፍላጎት ሲሰጧቸውም አንቀበልም ያሉባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እነዚህ ሰዎች አንቀበልም ያሉባቸውን አጋጣሚዎች ከነምክንያቶቻቸው እንመለከታለን፡፡

ነብዩ ዳንኤል

አንድ ጊዜ ብልጣሶር የተባለው የባቢሎን ንጉስ ለመኳንንቶቹ ባዘጋጀው ግብዣ ላይ ወይን ጠጅ ጠጥቶ ትንሽ ሞቅ ሲለው ታላቅነት ተሰማው፡፡ ከዚያም 'የቀበጡ ዕለት...' እንዲሉ ታላቅነቱን የሚገልጽ አንድ ነገር ለመስራት አሰበና አባቱ ናቡከደነጾር ከእየሩሳሌም የማረካቸውን የቤተመቅደሱን የወርቅና የብር እቃዎች በማስመጣት ከመኳንንቱ፣ ከሚስቶቹና ከዕቁባቶቹ ጋር በነሱ እየጠጣ እግዚአብሄርን 'ያንበረከኩትን' ከሚጠጣበት እቃ ጋር ከአንድ አይነት ጥሬ እቃ የተሰሩትን አማልክት አመሰገነ፡፡ ነገር ግን ታላቅነቱን ገልጾ ሳይጨርስ ወዲያው ከአፈር በተሰራ ግን አቅሙን ባላወቀ አንድ ሰው ስሙ የጎደፈበት አምላክ ራሱን ማስከበር እንደሚችል ለመግለጽ ንጉሱ በተቀመጠበት ትይዩ ባለው ግድግዳ ላይ "ላማ ቴቄል ፋሬስ" ብሎ ጻፈ፡፡ የብልጣሶር ፍስሃ በአንድ አፍታ ወደሽብር ተለወጠ፡፡ 'አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች' ነው ነገሩ፡፡ ጌታ እንዲህ ነው፡፡ 'ላማ ቴቄል ፋሬስ' የሚለው ሀረግ ምንም በወቅቱ ይነገር የነበረው አረማይክ ቋንቋ ቢሆንም እግዚአብሄር ንባቡንና ትርጉሙን ስለሰወረው ብልጣሶር ጠንቋዮችን መፈለግ ግድ ሆነበት፡፡ እነሱንም ትልልቅ ስጦታዎችንና ሽልማቶችን በማዘጋጀት ያለ የሌለ ጥበባቸውን ተጠቅመው እንዲያነቡና እንዲተረጉሙ ጋበዛቸው፡፡ ጌታ የቋጠረውን ማንም አዋቂ ነኝ ባይ አይፈታውምና እነሱም እንደሱው መረዳት ባለመቻላቸው የቋጠረው ጌታ ወገን የሆነውን ዳንኤልን ለመፈለግ ተገደደ፡፡ ዳንኤልም ተጠርቶ ከመጣ በኋላ ብልጣሶር ይህን ለሚፈታ ሰው የተዘጋጀውን ስጦታና ሽልማት ገለጸለት፡፡ ዳንኤል ግን ስጦታውን እንደማይቀበል በመግለጽ ጽሁፉን ወደመፍታት ተሸጋገረ (ዳን 5)፡፡

ብልጣሶር ቃል የሚገባለትን ስጦታ ዳንኤል መቀበል ያልፈለገው ለምንድነው? በውስጡ ያለው ምክንያትና መረዳት ምንድነው? መንፈሳዊ ሰው እንደመሆኑ 'አልቀበልም' ያለበት ምክንያቶችና የዛሬዎቹ መንፈሳውያን ሰዎች ከነዚህም የዳንኤል ምክንያቶች የምንማረው ምንድነው? መልሶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

አንደኛ ዳንኤል ነገር ለመፍታት የተመረጠ ሰው ነው፡፡ ይህን ቋጠሮ የመፍታት ስራ የሚሰራው ስራው ስለሆነ እንጂ ስጦታ ስለሚያገኝበት አይደለም፡፡ እኛ የእግዚአብሄር ሰዎች እንቆቅልሽ መፍታት ተልእኮአችን ነው፡፡ የምንሰራው በዚህ

ምድር ላይ የተቀመጥንበት ዓላማ ስለሆነ እንጂ በምላሹ ዋጋ ጠብቀን አይደለም። ለእኛ ስጦታው ሳይሆን ችግር መፍታታችን ብቻውን ርካታችን ነው። ዋጋም ከፈለግን ለፈታነው ችግር ትክክለኛውን ዋጋ ከሰማይ ካልሆነ ከሌላ ቦታ አናገኝም። እዚሁ ምድር ላይ ከሰው ከተቀበልን ግን ሰማይ ላይ የተቀመጠልን ዋጋ ይሟሟል (ማቴ 10:8)።

ሁለተኛ ለብልጣሶር የመጣው መልዕክት ስለአይሁድና ስለአይሁድ አምላክ ሲሆን የመልእክቱም ፍሬ ሃሳብ በብልጣሶር ላይ የእግዚአብሄር በቀል እንደሚመጣበት ነው፤ ዳንኤልም የተበቃዩ አምላክ የእግዚአብሄርና እግዚአብሄር የሚበቀልላቸው የአይሁድ ህዝብ ወገን ስለሆነ ከሚበቀለው ሰው ስጦታ መቀበል አልፈለገም። እንደመንፈሳዊ ተዋጊዎች ከምንበቀለው ነገር የምንወስደው ነገር ምርኮ እንጂ ስጦታ አይደለም። በአንድ በኩል እየጠላነው በሌላ በኩል ደግሞ ልክ እንደወዳጅ ከሱ ተጠቃሚ ልንሆን አንችልም። በሌላ ቋንቋ ተገለባባጭ መሆን አንችልም (ኢያ 6:18)፤ ቃሉም ይህን አይፈቅድልንም። እንዲፈርስና እንዳይሳካለት ከምንጸልይበት፣ እግዚአብሄር ከማይከብርበት እና ዓለማዊነት፣ ኃጢያትና አጋንንት ከነገሱበት ቦታ፣ ስራ፣ ሙያና ፖለቲካዊና ማህበራዊ ስርዓት ጥቅም አንጠብቅም። ይልቅስ ሰዎችን ሞት ካደፈጠበት ከዚያ ሁኔታ ውስጥ ነጥቀን በማዳን ምርኮን እንሰበስባለን። ባንድ በኩል እንዲጠፋ እየጸለይንበት ባንድ በኩል ከሱ የምንጠቀም ከሆነ ግን ጸሎታችን የመሰማቱ ነገር አጠራጣሪ ይሆናል።

ሶስተኛ ዳንኤል ከእንቆቅልሹ መፈታት የሚገኘው ክብር ለእግዚአብሄር ብቻ እንዲሆን ፈልጓል። ብልጣሶር ለጠንቋዮች ክብር እንደሚሰጥ ለሱም እንዲሰጠው አልፈለገም። መንፈሳዊ ሰው አገልግሎቱን መከበሪያ አያደርግም። የሚከብረው ላኪውና የጸጋው ባለቤት ጌታ ነው። አገልጋይ ተላላኪ ብቻ ነው (ሉቃ 17:10)።

አራተኛ ዳንኤል ከአመጸኛና እግዚአብሄርን ከሚደፍር ሰው ስጦታ መቀበልን ከሰውየው ስራ ጋር እንደመተባበር ቆጥሮታል። ከእግዚአብሄር ጠላት ስጦታን አለመቀበል ስራውንም አብሮ መጸየፍን እንደሚያሳይ ያመለክታል (ኤፌ 5:6)።

አምስተኛ ዳንኤል "የእግዚአብሄርን ጸጋ አልሸጥም አልለውጥም፤ እግዚአብሄርን የማገለግለው በነጻ ነው" የሚል አቋም አለው። ጸጋ ስጦታ ነው። ስጦታ ደግሞ አይሸጥም አይለወጥም። ለእርዳታ የሚመጣ የዩኤስኤይድ (የአሜሪካ ርዳታ ድርጅት) ዘይትና ስንዴ እንኳን "Not for Sale or Exchange" (አይሸጥም፤ አይለወጥም) የሚል ጽሁፍ ይጻፍበታል። ለምን? ለእርዳታ እንጂ ለንግድ የመጣ አይደለማ! ጸጋም ደካማ ስጋ የለበሰውንና በእሾክና አሜኬላ በተዋጠችው ምድር ውስጥ የሚኖረውን ሰው ለመርዳት የሚላክ ስጦታ እንጂ ለትርፍ ማግኛ የሚፈበረክ ሸቀጥ አይደለም። ከዚህም የተነሳ አገልጋይ ለገንዘብ የማይስገበገብና በነጻ የተቀበለውን በነጻ የሚሰጥ መሆን ይጠበቅበታል። አገልግሎት መጠቀሚያ ስላይደለ ካገለገሉ በኋላ እጅ መንሻና የአገልግሎት ዋጋ መቀበል አይፈቀድም (ዘሁ 16:15፤ 1ሳሙ 12:3፤ ሐዋ 20:33፤ ሐዋ 8:17-20)።

ዛሬ ግን ጸጋቸውን የሚቸረችሩ ብዙ ናቸው። ለአገልግሎት ሲጋበዙ እንኳን የሚሰጧቸውን አመስግነው ሊቀበሉ እነሱ ራሳቸው "ይህን ያህል ገንዘብ ትከፍሉኛላችሁ፣ የምትወስዱኝ በእንዲህ ያለ መኪና ወይም በአውሮፕላን ነው፣" ወዘተ የሚሉና አስቀድመው የሚደራደሩ ጥቂት አይደሉም። በአጋጣሚ አስቀድመው መደራደር ካልቻሉ ደግሞ አገልግለው ሲጨርሱ የሚሰጧቸውን ገንዘብ ከቆጠሩ በኋላ ትንሽ መስሎ ከታያቸው መልሰው የሚወረውሩ እንዳሉ አይተናል። ይህ ከጸጋው ጋር ታሽጎ ከተሰጠን የአጠቃቀም መመሪያ (manual) ጋር ይጣረሳል። የተባልነው "በከንቱ ተቀበላችሁ፤ በከንቱ ስጡ" (ማቴ 10:8)፤ "ኤጲስ ቆጶስ ገንዘብን የማይወድ ሊሆን ይገባዋል" (1ጢሞ 3:3) ነው።

ስድስተኛ ዳንኤል ሊሞት ከተወሰነበትና መንግስቱ ካለቀ ንጉስ ስጦታና ስልጣን መቀበል ትርጉም እንደሌለው ገበቶታል። ዳንኤል የተረጎመው የእግዚአብሄር ጽሁፍ የብልጣሶር መንግስት እንደተቆረጠና ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎች እንደተሰጠ የሚናገር ነው። መልእክቱ በተነገረ እለት ማታ ብልጣሶር እንደተገደለም እናነባለን። ታዲያ እንዲህ ካለው ሰው ስልጣን መቀበል ምን ትርጉም አለው? ምናልባትም አብሮ መገደልም ሊመጣ ይችላል እኮ? ስለዚህ ስልጣኑን ከመቀበል ይልቅ ቢቻል የሚመጣው መንግስት እንደብልጣሶር ያለ እጣ እንዳይገጥመው ለመርዳት መዘጋጀትና ከሚመጣው አሰራር ጋር እንዴት አብሮ መሄድ እንደሚቻል ማሰብ የተሻለ ነው።

የዛሬዎቹ የእግዚአብሄር ሰዎችም እንደዳንኤል ዘመኑን እንመርምር፡፡ ባለቀ ሰዓት ልባችን በምድር ውስጥ ባሉ ነገሮች አይወሰድ (ነቆሮ 7፡29-31)፡፡ ጌታ ሊመጣ በደጅ ነው፡፡ ይህችም ዓለም በመቃጠል ልትጠፋ ጊዜው ቅርብ ነው (2ጴጥ 2፡10)፡፡ ዛሬ ልባችንን ለመስለብ ላይ ታች የሚለውና በብልጭልጭ ነገር እያባበለን ያለው በዮሀንስ ራዕይ ላይ እንደተባለው ከዚህ በኋላ ያለው ዘመን ጥቂት እንደሆነ ተገንዝቦ ወደምድር ተጣድፎ የወረደው የዚህ ዓለም አምላክ ዲያብሎስ ነው፡፡ ማዘናጊያውን አንቀበል (ራዕ 12፡12)፡፡

ነብዩ ኤልሳእ

በመጽሃፍ ቅዱሳችን ውስጥ ለአገልግሎቱ ዋጋ አልቀበልም ሲል ዳንኤል የመጀመሪያ ሰው አይደለም፡፡ ከእሱ በፊትም ኤልሳእ የሚባለው ነቢይ በአገልግቱ ንእማን የተባለው የሶሪያ ሰራዊት አለቃ ከለምጹ ከተፈወሰ በኋላ ያቀረበለትን ስጦታ እምቢ ብሏል (2ነገ 5)፡፡ ንእማን የሚባል የተከበረ የሶሪያ ጦር አዛዥ ለምጽ ነበረበት፡፡ በቤቱ የምትኖር አንድ እስራኤላዊ ምርኮኛ ብላቴና እስራኤል ውስጥ ለፈውስ ሊጸልይለት የሚችል ነብይ እንዳለ ነግራው ከሶሪያ ንጉስ ደብዳቤ አስጽፎ እና ስጦታ ይዞ ወደእስራኤል ንጉስ ሄደ፡፡ የእስራኤል ንጉስ የፈውስ አገልግሎት ስለማይሰጥ ንእማን ያመጣውን የፈውስ ጥያቄ እንደነገር ፍለጋ ወሰደው፡፡ ስለዚህም በወቅቱ በነበረው ባህል በጣም የተናደደ እና ያዘነ ሰው ልብሱን በመቅደድ ስሜቱን ይገልጽ ስለነበር ልብሱን ቀደደ፡፡ በርግጥ የሶሪያ ንጉስ ደብዳቤውን ለእስራኤል ንጉስ የጻፈው ወደነብይ ወርዶ ከመነጋገር በደረጃው ካለው ንጉስ ጋር ለመነጋገርም አስቦ ይሆናል፡፡ ቢሆንም እሱ ደረጃውን ሲጠብቅ በተዘዋዋሪ በነቢዩ ውስጥ ያለውን እግዚአብሄርን እየናቀ ነበር፡፡ ኤልሳእ ግን በኩራት "ልብስህን ለምን ቀደድህ ወደ እኔ ይምጣ፤ በእስራኤልም ዘንድ ነቢይ እንዳለ ያውቃል ብሎ ወደ ንጉሡ ላከ።" በርግጥ ንእማን ነገር ለመፈለግ ባይመጣም ነቢዩ ይህ አጋጣሚ ለሶሪያውያን የእግዚአብሄርን ክብርና ማንነት ማሳያ እንደሚሆን በመንፈስ አስቧል፡፡ እስራኤል የምትመራው እንደሶሪያ በምድራዊ ንጉስ ብቻ እንዳይደለ እና የክብሯ ምንጭ ምድራዊ ሀይል እንዳልሆነ ለማስመስከር የተዘጋጀ ጊዜ ነበር፡፡ ኤልሳእ ባቀረበው ሀሳብ መሰረት ንእማንን ወደኤልሳእ መጣ፡፡ መጀመሪያ ለመቀበል ቢቸግረውም ኤልሳእ በነገረው መሰረት ዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ብሎ ተፈውሰ፡፡ ከዚም ንእማን የፈወሰውን ጌታ እግዚአብሄርን ወደማምለክ አዘነበለ፡፡ ነገር ግን ኤልሳእ ስጦታውን አልተቀበለም፡፡ ኤልሳእ የተናገረው ንግግርና የንእማን የአመጣጥ ሁኔታ በሚጠቁመው መሰረት የቀረበለትን ዋጋ ያልተቀበለባቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

አንደኛ ኤልሳእ ለንእማን የሰጠው የፈውስ አገልግሎት እግዚአብሄር የእስራኤል አምላክ እስራኤልም የታላቁ አምላክ የእግዚአብሄር አገልጋይ እንደሆነ ለማሳየት የተደረገ ነው (2ነገ 5፡8)፡፡ ሶርያውያን በወቅቱ ከነበራቸው ኃይል የተነሳ እስራኤልን ይንቃሉ (1ነገ 21፡1-10፣28)። የእግዚአብሄርን ህዝብ ናቁ ማለት ደግሞ እግዚአብሄርን ናቁ ማለት እንደሆነ 1ተሰ 4:8 ላይ ተጽፏል፡፡ ንእማንም ቢሆን የሶሪያ ጦር መሪና የከፍታቸው ምክንያት ስለሆነ (1ነገ 21፡1) ይህን ስሜት መጋራቱ እሙን ነው፡፡ ስለዚህ ለኤልሳእ ‘ታላቅ ነን’ በሚሉና ሌላውን በሚንቁ ሰዎች ዘንድ ጌታ መታወቁ ብቻውን ዋጋው ነው፡፡ ንእማን በአገሩ ታላቅ ቢሆንም እስራኤል ያለውን የታላቆች ታላቅ እግዚአብሄርን ግን ዝቅ ብሎ ለማምለክ በለምጹ ምክንያት ተገደደ፡፡ በዚህም በእስራኤል ዘንድ ቸል የማይባል አንድ ትልቅ ነገር እንዳለ ተገነዘበ፡፡ ከዚህ በኋላ እስራኤልንና እግዚአብሄርን መናቅ አያስኬደውም፤ አያዋጣውምም፡፡

እኛም በዚህ ምድር ስንኖር ሳለ ከክርስትናና ከክርስቲያን ቁም ነገር የማይጠብቁና ክርስትናን ሞኝነት አድርገው የሚቆጥሩ፣ ወይም በሌላ ጎኑ ክርስቲያንን የሚጠሉ፣ ክርስቲያን ሲያዩ ፊታቸው የሚንጠለጠልና ቢችሉ ከክርስቲያን ነጻ በሆነች ምድር ለመኖር የሚፈልጉ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ማመናቸው ለኛ ትልቅ ዋጋ ነው፡፡ የሚኮሰኩሰው ፊታቸው መለስለሱና የተንጠለጠለው መሰተሩ ለኛ ውጤት ነው፡፡ በናቁት ጌታ እጅ መውደቃቸው ለኛ ሽልማት ነው፡፡

ለኤልሳእ ሁለተኛው ዋጋው በእግዚአብሄር ሀገር ያለው ወንዝ ሳይቀር አህዛብ አገር ካሉት ወንዞች ጋር ተወዳድሮ ማሸነፉ ነው፡፡ ኤልሳእ የንእማንን ስጦታ አልቀበልም ሲል እስራኤላውያን ከሶሪያ የሚፈልጉት እንደሌለና ቆሻሻ የተባለው ውሃቸው እንኳን ከሶሪያ ወርቅ፣ ብርና ምርጥ ልብስ የከበረ እንደሆነ መልዕክቱን ማስተላለፉ ነው፡፡ ሶሪያ ያሉት አባናና

ፋርፋ የተባሉት ወንዞች ከዮርዳኖስ በንጽህና የተሻሉ ቢሆኑም ፈውስን ግን መስጠት ስለማይችሉ ንእማን ድፍርሱ ዮርዳኖስ ውስጥ ገብቶ መታጠብ ግድ ሆነበት፡፡ ለካ የተናቀውና ሲያዩት የማያምረው ሁሉ በእግዚአብሄር ህዝብ እጅ ውስጥ በመሆኑ ብቻ እጅግ የተከበረ ነው!

ጌታ ያለባትና የባረካት የኛ ትንሽና የተናቀች ነገር ጌታን ከማያውቅ ሰው ብዙ መዝገብ ትበልጣለች፤ ታስደስታለች (መዝ 84፡10)፡፡ በጌታ ህዝብ ዘንድ "ሲያዩት ያላማረ ..." የሚለው አባባል አይሰራም፡፡ ጌታ ካለበት ትንሽ፣ የማያምር፣ የማይማርክ የሚባል ነገር የለም፡፡

በተጨማሪ ኤልሳእ ስጦታውን አለመቀበሉ "እስራኤል ባለነቢይ መሆኑ ብቻ ብዙ ሀብትና ትልቅ ክብር አለን ከምትሉት ከእናንተ ከሶሪያውያን ያስበልጠዋል" ማለቱ ነው፡፡ "እኛ ነቢይ ካለን እግዚአብሄር አለን፤ እግዚአብሄር ካለን ደግሞ ሁሉ አለን፤ ከሌላ ሀገር የምንፈልገው ነገር የለንም" ማለቱ ነው፡፡ ይህም መልእክቱ ውጤታማ መሆኑን የምናየው ንእማን ለእግዚአብሄር መሰዊያ ለመስራት ከእስራኤል አፈር ለመውሰድ ሲለምን ነው፡፡ ስለዚህ ኤልሳእ እስራኤል እንደሚሰጥ እንጂ እንደማይቀበል አስመሰከረ፡፡ እግዚአብሄር ካለን ከአለም ሁሉ የሚበልጥ ነገር አለን ማለት ነው፡፡ ሌላ ነገር አያሻንም፡፡

ሁለተኛ ኤልሳእ ልክ ከወዳጁ እንደሚወስድ ከጠላቱ ስጦታ መቀበል አልፈለገም፡፡ ሶርያውያን ለእስራኤል ጠላቶች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ አደጋ ይጥሉባቸዋል፡፡ ታዲያ ከጠላት ልክ እንደወዳጅ እንዴት ስጦታ ይወሰዳል? ይልቅስ ከዚህ በኋላ ጠላትነቱ ወደእፍረት እንዲለወጥ ማድረግ ነው የሚገባው፡፡ ኤልሳእ የንእማንን ስጦታ አልቀበልም ሲል አእምሮ ውስጥ ይህ ሀሳብ እየተመላለሰ ያለ ይመስላል፡፡

የጌታ ሆነን ሳለ የሚጠሉን ካሉ እንዴት ከነሱ ስጦታ እንጠብቃለን? ማድረግ ያለብንማ ከዚህ በኋላ ሊጠሉን እንደማይችሉ ማሳየት ነው እንጂ! እነሱ የሌላቸው ትልቅ ነገር (ታላቁ ጌታ እና እሱ የሚሰጠው ጸጋ) እኛ ጋር እንዳለ በማሳየት እኛን የሚጠሉበትንና የሚመኩበትን ሁሉ ከንቱ እናደርገዋለን እንጂ! ከነሱ እንደምንበልጥና ከነሱ አንዳች እንደማንፈልግ እናሳያቸዋለን እንጂ! ያውም እጃችን ላይ ወድቀው? ጌታችንንማ እናስከብረዋለን!

ሶስተኛ ጊዜው እግዚአብሄርን ማስከበሪያ እንጂ ዋጋ መቀበያ አይደለም፡፡ የንእማን እግዚአብሄርን ማምለክ መፈለግ በቂ ዋጋ ነው፡፡ ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች በረከት የምንለውን ሁሉ ከመሰብሰባችን በፊት ይህ ጊዜ በርግጥ በረከት የምሰበስብበት ጊዜ ነው? በዚህ ጊዜ በረከት ብቀበል ነው ወይስ ባልቀበል ጌታ የሚከብረው? ብሎ መጠየቅ ጥሩ ነው፡፡

አራተኛ የንእማን አመጣጥ በሁለት መልኩ ትክክል አልነበረም፤ አንዱ ስህተቱ ፈውስ በዋጋ ሊገዛ መምጣቱ ሲሆን ያመጣውን ስጦታ ኤልሳእ ቢቀበለው የሚሰጠው ትርጉም ፈውስን በዋጋ ገዝቶ እንደሄደ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ስጦታው ተቀባይነት ቢያገኝ ኖሮ በስጦታ ውለታውን እንደመለሰና እዳ እንደሌለበት ስለሚያስብ እግዚአብሄርን ለማምለክ ዝንባሌው አያድርበትም ነበር፡፡ ይህ ደግሞ እግዚአብሄር በንእማን ዘንድ እንዲኖር የሚፈልገው መረዳትና ዝንባሌ አይደለም፡፡ ሁለተኛው ስህተቱ የመጣው የእግዚአብሄርን ፈዋሽነት ይህን ያህል አምኖበት ሳይሆን ሌላ መፍትሄ ስላጣ እንደመጨረሻ አማራጭ ለመሞከር ነው፡፡ ስለዚህ ሳያምን ሊሰጥ ከሚፈልግ መቀበል ጌታን ስለማያስከብረው ኤልሳእ እምቢታን መረጠ፡፡

በተሳሳተ አመለካከት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማስተካከል የምንችለው ከተሳሳተ አመለካከት ከመነጨው ድርጊታቸው ጋር ባለመተባበር ነው፡፡ ከመተባበር የምንድነው ደግሞ ከሰዎች ድርጊት ጀርባ ያለውን አመለካከታቸውን መመርመር ስንችል ነው፡፡ ምንም እንኳ ድርጊቱ የሚነቀፍ ባይሆንም ከጀርባው ያለው አመለካከት ከጌታ ሃሳብ ጋር የማይስማማ ከሆነ ድርጊቱ ለጌታ ክብር ስለማይሆንና መንፈሳዊ ትርፍ ስለሌለው እንዲያውም ሌላ ጎጂ ነገር አስከትሎ ሊመጣ ስለሚችል አለመተባበሩ መንፈሳዊነት ነው፡፡ ለምሳሌ ለባእድ አምልኮ የተዘጋጀን ምግብ መብላት ለምን ይጠላል? ተመሳሳይ ምግብ እኛ ቤትስ ይዘጋጅ የለ እንዴ? ችግሩ እነዚያን ባእድ አምልኮ ውስጥ ያሉትን ሰዎች አሉበት እንዲቆዩ ስለሚያበረታታና ራሳቸውን እንዳያዩ ስለሚከለክል ነው፡፡ ካልበላንላቸው ግን እነሱ እንደተሳሳቱ እኛ ግን የገባን አንድ ምስጢር እንዳለ ይገነዘባሉ፤ ከበረቱም ወደጌታ ይመጣሉ፡፡

አምስተኛ ንዕማን አክብሮት ይፈልጋል (ቁ 11)፤ ራሱን ከሚያከብር ደግሞ ስጦታ መቀበል እግዚአብሄርን አያስደስትም፡፡ መጀመሪያም ኤልሳእ ይህን የንእማን ኩራት

በመንፈስ ስላየ ወደሱ ሳያስቀርበው በዚያው በሩቁ ነው ወደዮርዳኖስ ሄዶ ብቅ ጥልቅ እንዲል የነገረው።

በርግጥ መጽሀፉም ክብር ለሚገባው ክብርን እንድንሰጥ ስለሚያዘን (ሮሜ 13፡7) መንፈሳዊ ሰው ሰውን እንደሚገባው ማክበር ይጠበቅበታል። ነገር ግን ከሚገባው በላይ ክብርን ለሚፈልግ ሰው ከሱ በላይ የተከበረ እንዳለ ማሳየት ኃላፊነታችን ነው። እኛ የተከበረው ጌታ አፈ-ቀላጤዎች፣ ጉዳይ አስፈጻሚዎችና እንደራሴዎች ነን። ስጦታ የሚያቀርብልንን ስጦታውን ከክብሩ ጋር ለራሱ በመተው ከኛ ጋር ያለው የጌታን ክብር እናስጠብቃለን። ከኩራት የመነጨ ስጦታ ለኛ በረከት አይሆንልንም። ክርስቲያን ትሁት እንጂ ሽቁጥቁጥ አይደለም።

ሀዋርያው ጳውሎስ

በአዲስ ኪዳንም የመስጠት መቀበል መርሁን የሻረ አንድ ሰው እንመልከት ። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ቀለብ አልቀበልም ብሏቸዋል (1ቆሮ 9፡1-3፣15-18)። እንደህጉ ከሆነ አገልጋይ ወንጌል ሲያገለግል ያገለገላቸው ደግሞ በኑሮው እንዲደግፉት ይገባ ነበር። ነገር ግን መደገፍ የሚገባቸው ሰዎች መደገፉን አምነውበት፣ መንፈሳዊ ግዴታቸው መሆኑን አውቀው በቅንነት ካላደረጉለት ጉዳቶች አሉት። ጳውሎስም ከቆሮንቶስ አማኞች ቀለብ አልቀበልም ያለው እነዚህ ጉዳቶች እንዳይደርሱበት ነው።

አንደኛ ቢቀበል በወንጌል ሰራተኝነቱ ያለው ኩራት ከንቱ ይሆንበታል። እውነተኛ የወንጌል አገልጋይነቱ ጥያቄ ውስጥ እንዳይገባበት በነጻ ማገልገልን መርጧል። የሚሰጡትን ቀለብ እንደደመወዝ ከቆጠሩት ደስታ አይሰጠውም። አገልግሎቱን ሰጥቶ ከመቀበል ጋር ካያያዙበት ወይም እሱ እስከህይወት መስዋትነት ወስኖ የሚደክመውን ድካም ዋጋ ከማግኘት ጋር ካያያዙበት በአገልግሎቱ ነጻነት አይሰማውም። ለአገልጋዩ የህሊና ቁስል ነው። ስለዚህ ተቀጣሪነት ከሚሰማው እና ለወንጌል ቆርጦ መውጣቱን በዜሮ ከሚያባዛበት አለመቀበሉን መምረጥ ግድ ሆነበት።

ሁለተኛ ለአገልግሎቱ መሰናክል ይሆንበታል። ተገልጋዮቹ ለገንዘብ እንደሚሰራ፣ ስራ ሲፈታ ወደወንጌል ስራ እንደዞረ፣ ወዘተ እያሰቡ ለመልእክቱ ትኩረት አይሰጡም። መልእክቱ ክብደት ያጣል (ቁ 12)። በተለይ የሚቀኑበት፣ የሚፎካከሩት እና አገልግሎቱ ቢሰናከል ደስ የሚላቸው ሰዎች እንዳሉ እና ለዚህም ፍላጎታቸው መሳካት ስሙን በማጥፋትና በመክሰስ የተጠመዱ ሰዎች እንዳሉ በፊል 1፡ 16-17 ላይ ተገልጾአል። ስለዚህ የወንጌሉ መስፋፋት በዚህ ሰበብ ከሚጓተት አለመቀበሉን መረጠ።

ሶስተኛ በጌታ ዘንድ ያለውን ደመወዝ ከንቱ ያደርግበታል። መብትን መጠቀም ጥሩ ቢሆንም መብቴ ነው እያሉ መቀበሉ ከመንጠቅ አይሻልም። የወንጌል ስራ የሚራው ከመብት ይለቅ በፍቅር ነው። በሰማይ ዋጋ ያለው በፍቅር የተሰራ ብቻ ነው። መብት የሚሆነው አገልጋዩ እና ተገልጋዩ አንድ በምድር ላይ ርስ በርስ በመደጋገፍ መርህ በተመሰረተ ህብረት አባል በመሆናቸው የተነሳ እና አገልጋዩ ስራ ስለማይሰራ እና የማይሰራ ምግቡን ማግኘት እንደማይችል የተቀመጠውን መርህ ስለሚገዛቸው ነው። ሁለቱም እግዚአብሄር በምድር ላይ ሳለን እንድንመራባቸው ያስቀመጣቸው መርሆች ናቸው። ከላኪው ከእግዚአብሄር ጋር ባለው ግንኙነት አንጻር ካየው ግን መብቱን የሚጠይቀው ከእግዚአብሄር ነው። ጳውሎስን መጠቀም የፈለገው እግዚአብሄር ጳውሎስ ላጠፋው እድሜው ማካካሻ መክፈል አለበት። ያን ማካካሻ እንዳያጣ ስለ እግዚአብሄር ሆነው ሊከፍሉት ካሉት ሰዎች ጋር የገባውን ውል መሰረዝ አለበት።

እነዚህ ሶስት የጳውሎስ ምክንያቶች ለዛሬ አገልጋዮችም ይሰራሉ። አገልግለን የሚሰጡንን ከመቀበላችን ጋር ተያይዘው እነዚህ ጉዳቶች የሚደርሱ ከሆነ አለመቀበሉ የተመረጠ ነው። በተጨማሪ በአይናችን የምናያቸው፣ በምስክርነት የሰማናቸው እና በህይወታችን የደረሱ ከመስጠት ጋር የተያያዙ ሌሎች ጉዳቶች አሉ።

ሀ. አንዳንድ ተገልጋዮች ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአገልጋዩ ገንዘብ ሰጥተው እንደልቡ ሳይሆን እንደልባቸው እንዲያናገለግል እዳ ውስጥ ያስገቡታል። በገንዘቡ አፉን ይለጉሙታል። በገንዘብ ምክንያት በእግዚአብሄር ተጠርቶ የሰው አገልጋይ ሆኖ ይቀራል።

ለ. አገልጋዩን እንደረዱ ቆጥረው ራሳቸውን ያመሰግኑበታል። ሰርቶ ማግኘት ይችል የነበረውን

ሰው በዚህ መንገድ ለጌታ ብሎ መውጣቱን ረስቶ ተረጂነት እንዲሰማውና የሚቀበለውን እንዲንሸማቀቅበት ያደርጉታል፡፡

ሐዋርያው ጴጥሮስ

ጳውሎስ የመስጠት መቀበል መርሁን የሻረ ብቸኛው የአዲስ ኪዳን ሰው አይደለም፡፡ ጴጥሮስም በሰዎች ላይ እጁን ጭኖ መንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ከጥንቆላ አለም የመጣው ሲሞን የተባለ ሰው አይቶ ከዱሮ ህይወቱ እንደለመደው ከፍያ አምጥቶ ይህ መንፈስ ቅዱስን "የመሙላት ጥበብ" እንዲሰጠው ጠየቀ፡፡ ጴጥሮስ ግን አልቀበልም ከማለትም ባለፈ ሲሞንን ፈረደበት፡፡ የአለመቀበሉ ምክንያት መንፈስ ቅዱስን መሞላት ከእግዚአብሄር የሚደረግ የነጻ ስጦታ እና አገልጋዮቹም በነጻ እንዲጸልዩ የተሰጣቸው ሀላፊነት ስለሆነ ነው (ሀዋ 8፡18-21)፡፡

ጴጥሮስ አልቀበልም ያለው ቁስ ብቻ አይደለም፡፡ ከብርንም ገፍቷል (ሀዋ 10፡26)፡፡ ወደቆርኔሌዎስን ቤት ሊያገለግለው ሲሄድ ቆርኔሌዎስ ሲሰግድለት "ተነሣ፤ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ" ብሎ ሊሰግድለት እንደማይገባ እና ስግደቱን እንደማይቀበለው ተናገረ፡፡ ጴጥሮስ ከጌታው የተማረው የማልጠቅም ባሪያ ነኝ (ሉቃ 17፡10) እንዲል እንጂ ራሱን እንደምርጥ አገልጋይ ቆጥሮ ለምርጦች የሚገባ ክብር እንዲቀበል አይደለም፡፡ ክብር የሚገባው ይህን የተከበረ ስራ ለማይገባቸው ሰዎች የሰጠ እግዚአብሄር ብቻ ነው፡፡ አገልጋይ በጌታ ችሮታና ምህረት እንደሚያገለግል መርሳት የለበትም፡፡ በሸክላ እቃ ውስጥ የከበረ መዝገቡን ለማስቀመጥ በደፈረው ጌታ እየተደነቀ እና እያመሰገነ ይህንንም ለተገልጋዮቹ እያስረዳ ያገልግል፡፡

እነዚህ አገልጋዮች ልባም ሆነው አንቀበልም በማለታቸው ተጨማሪ የከፉ ችግሮችንም ተከላክለዋል፡፡ ኤልሳእ ቢቀበል ኖሮ በተቀበለው በግያዝ ላይ እንደሆነው ንእማን ላይ የነበረው ለምጽ እሱ ላይ ሊወጣበት ይችል ነበር፡፡ የኩራተኛ ገንዘብ የኩራተኛውን ባህሪ እና የኩራቱን ውጤት የተሸከመ የመርገም እቃ ነው፡፡ ከኩራተኛዋ የኢያሪኮ ከተማ የተወሰደ ነገር ለአካን የኩራተኛዋ ከተማን እጣ ፈንታ እንዳመጣበት አይረሳም (ኢያ 9)፡፡ ችግር ካለባቸው ሰዎች በሰጥቶ መቀበል መርህ የምንወስዳቸው ነገሮች ወደእኛ የሚመጡት ከነሰዎቹ ችግር ነው፡፡ ጴጥሮስ በጥንቆላ የተሰበሰበውን የሲሞንን ገንዘብ ቢቀበል ኖሮ ለመንፈስ ቅዱስ መሰጠት ምክንያት የሆነው ሰው የርኩስ መንፈስ ተቀባይ ይሆን ነበር፤ እንዲሁም ሲሞንን በረገመበት የጥፋት መርገም ይመታ ነበር፡፡ ከጥንቆላ የተገኘ ገንዘብ ከነድምጥማጡ ይጠፋል እንጂ አይዋጅም (ዘዳ 12፡3፤ ዘዳ 7፡25-26)፡፡ ቀድሞ ካልጠፋ ይዞ ይጠፋል፡፡

ስለዚህ ክርስቲያን ሆይ አንተም እንደዳንኤል፣ እንደኤልሳእ፣ እንደጳውሎስ እና እንደጴጥሮስ “አልቀበልም” የሚል ድፍረት እንዲኖርህ አምላክህ ይፈልጋል፡፡ ዳንኤል፣ ኤልሳእ፣ ጳውሎስ እና ጴጥሮስም እንዳንተ ሰው ነበሩ፡፡ ***ተፈጸመ፡፡***

የቤርያ ቁጥር 13 ጥያቄዎች መልሶች

1. በአመጽ ከሚገኝ ከብዙ ትርፍ ይሻላል፡፡ (ምሳ 16፡8)
2. የከብር ዘውድ ነው፡፡ (ምሳ 16፡31)
3. ከተማ ከሚወስዱ ይበልጣል፡፡ (ምሳ 16፡32)
4. የእግዚአብሄር መብራት ነው፡፡ (ምሳ20፡27)
5. እንዳንበሳ ያለፍርሃት ይኖራል፡፡(ምሳ 28፡1)

አዘጋጅ - አበበ መንግሻ (ዶ/ር)
ስ.ቁ. – 0936669160 ኢሜይል - abebe.meng@gmail.com
ፌስቡክ ገጽ - Berea teaching
ቴሌግራም https://t.me/bereamagazineethiopia
መጽሄቱን በኢሜይል በመላክ እና ኮፒ አድርገው በማደል ሌሎች ሰዎችም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
የቀድሞ እትሞችን በቴሌግራም ቻነል ላይ ያገኛሉ፡፡

የቤርያ ጥያቄዎች

1. አሞጽ ለነብይነት ሲጠራ ስራው ምን ነበር?
2. በማረስ ላይ እያለ ወደአገልግሎት የተጠራ ነቢይ ማነው?
   ሀ) ኤርምያስ ለ) ኤልሳዕ ሐ) ዳንዔል መ) ዮናስ
3. በኢየሱስ የዘር ሃረግ ውስጥ የገቡ ከአህዛብ ወገን የሆኑ ሴቶች እነማናቸው?
4. ጳውሎስ እንደአምላክ ተቆጥሮ የወጣለት ስም ማነው?
5. ዳዊት ሜልኮልን ለማግባት የጣለው ጥሎሽ ምንድነው?

(መልሱን በቁጥር 15 ላይ ያገኛሉ)